# ቅኝት

# የተማሩ ማይማን

## ትምህርት ከነቢብ እስከ ገቢር

በበፍቃዱ ኃይሉ፣ ቅ/ማ/ዩ/ኮ



በዚህ ርዕሰ ጉዳይ የመጻፍ የረዥም ጊዜ ዕቅድ ይገፘ የነበረ ቢሆንም፥ የአዲስ ጉዳይ መጽሔት ዐምደኛ የሆነው ዲያቆን ኤፍሬም ‘ፊደል የቆጠሩ ማይማን’ በሚል ርዕስ ተመሳሳይ ፅንሰ ሐሳብ ያለው መጣጥፍ በመጻፉ ዕቅዴን ለመቀየር ደርሼ ነበር፡፡ ሆኖም ደጋግሜ ሳስበው በአንድ በኩል ስለርዕሰ ጉዳዩ ገና ብዙ የሚባል ነገር በመኖሩ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ኤፍሬም ጉዳዩን የተመለከተበት ማዕዘን የተለየ ስለሆነ ጉዳዩን በውጥን የመተዌን ሐሳብ ትቼው እነሆ መጻፍ ጀምሬያለሁ፡፡

የተማሩ ማይማን የሚለው ሐረግ ፈረንጆቹ ‹Functionally Illiterates› የሚሏቸውን እንዲተካ የጸሐፊው ብርቱ ፍላጎት ነው፡፡ ሆኖም ከዚያ የበለጠ አንድምታ ቢኖረውም አይከፋም፡፡ (እሱን እየሄድን እንወስናለን) ዊኪፔድያ የተባለው ድረዓምባ ‹Functional Illiteracy›ን ‘የማንበብ እና የመጻፍ ክህሎቱ ከማንበብ እና ከመጻፍ ባሻገር ለተግባር የማያበቃ’ በሚል ይበይነዋል፡፡ ከመሠረታዊ የንባብ ደረጃ ከፍ ብሎ ለሥራ የማያበቃ የንባብ ችሎታ እንደማለት ነው፡፡ እኔም የተማሩ ማይማን በሚል ለሰጠሁት ርዕስ ተቀራራቢ ብያኔ (definition) አለኝ፡፡

የተማሩ ማይማን የተማሩትን ትምህርት በኀልዮት (theory) ከማነብነብ ውጪ በተግባር የማያስመሰክሩ ምሁራንን ይወክላል፡፡

በሀገራችን ከዘመን ዘመን እያደገ የመጣ ለትምህርት የመጓጓት ዝንባሌ ይታያል፡፡ ምሁራን በማኅበረሰቡ አንቱታን ይቸራሉ፡፡ ማይማን ለመማር፣ የተማሩትም የበለጠ ለመማር ይጓጓሉ፡፡ ነገር ግን ከሚማሩትም ሆነ ከተማሩት መካከል ጥቂት የማይባሉትን ካስተዋልን፥ በትምህርቱ ከሚያፈሩት ዕውቀት ይልቅ በሰርተፍኬቱ የሚያገኙትን ውዳሴ ያስቀድማሉ፡፡ የዶክትሬት ጥናቱ ካስተማራቸው ቁም ነገር ይልቅ ማዕረጉ ያኮራቸዋል፡፡

በመሠረቱ በልፋት በተገኘ ውጤት መኩራት ሊተች የሚገባው ነገር ሆኖ ብዕሬን ለማሾል አልተቻኮልኩም፡፡ ውስጤን እየኮረከረ እንድጽፍ ያነሳሳኝ ዐቢይ ጉዳይ ግን ከላይ የጠቀስኳቸው ዓይነቶቹ ‹ምሁራን› በተግባርና ሊጨበጥና ሊዳሰስ በሚችል መልኩ ‹ምን እየሠሩ ነው?› የሚለውን በወፍ በረር መቃኘት ስለፈለግሁ ነው፡፡ ዓመት ሙሉ በምንም ዓይነት ጥናት ላይ ያልተሳተፈ ዶክተር፣ ስለ ትንባሆ ማጨስ ጠንቀኝነት የሚያስተምር አጫሽ፣ ስለትራፊክ ደህንነት የሚያስተምር ነገር ግን የትራፊክ ሕግጋትን የሚጥስ ‘ሳጅን’ እና የመሳሰሉትን፥ ‘የተማሩ ማይማን’ ያሰኘሁት ጽሑፍ ይመለከታቸዋልና ያንብቡት፡፡ ማን ያውቃል - ከልብ ካለቀሱ እንደሚባለው የ‹በኛ ይብቃ፤ትውልድ ይዳን› መፈክር በነሱም ዘንድ ጎራ ሊል ይችል ይሆናል፡፡

ከዚያ በፊት ግን የእኛን አገር የተማሩ ማይማን ሳጣቅስ ጉዳዩ የአገር ውስጥ ብቻ ነው እያልኩ ለሚመስላቸው ሰዎች እንዲያውቁልኝ የምፈልገው ነገር አለ፡፡ ለምሳሌ ‹TIME› መጽሔት በኦገስት 14፤ 1989ዓ.ም. ዕትሙ በብዛት አንድ ሦስተኛ የሚሆኑት የ17ዓመት አሜሪካውያን የተማሩ ማይማን ናቸው ሲል ጽፏል፡፡

እኔ በዚህ ጽሑፍ የሀገራችንን ምሁራን የምወቅሰው በከፍተኛው የትምህርት ቁንጮ ላይ ደርሰው እንኳን ማዕረጋቸውን የሚያስመሰክር አንባቢነትና ጸሐፊነት ይጎድላቸዋል በሚል ነው፡፡ (የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀው ብቻ የተቀመጡትን ብዙ አንጠብቅባቸው ብንል እንኳን ማለቴ ነው፡፡)

## አንባቢነት

አንድ ምሁር፤ በተማረበት ዘርፍ፣ ተማሪ በነበረበት ወቅት ብቻ ያነበነባቸውን ብያኔዎችና ትንታኔዎች ብቻ እያስታወሰ በሥራ ዓለም ውጤታማ ሆኖ ለዓመታት መዝለቅ አይቻለውም፡፡ ዕውቀት ወይም ክህሎት እንደቁሳቁስ ሁሉ ከጊዜ ጋር ሊሸረሸር (depreciate ሊያደርግ) ይችላል፡፡ ማንኛውም የትምህርት ዘርፍ ከጊዜው እኩል አዳዲስ ግኝቶች እየተደመሩበት እየተሻሻለ መምጣቱ የማይቀር ስለሆነ ምሁራን በሙያቸው ያላቸውን ዕውቀት በተመሳሳይ መንገድ እያሳደጉ፣ የለውጡ ወይም የመሻሻሉ አካል መሆን ካልቻሉ ማዕረጋቸው ብቻውን እራሳቸውንም አገራቸውንም መለወጥም ሆነ መጥቀም አይችልም፡፡

በእኛ አገር፣ ማንበብ አስነዋሪ የሆነ ይመስል ብዙ ምሁራን ከማይማን የማንበብ ደረጃ እንኳን ባነሰ አሽቆልቁለው የመገኘታቸው ምሥጢር ዕንቆቅልሽ ነው፡፡ ነገሩ የሚጀምረው ከልጅነታዊ አስተዳደጋችን ቢሆንም ዐውቀንም የምንለውጠው አይመስልም፡፡ አሁን አሁን የከፍተኛ ተቋማት ተማሪ ሆኖ በሚማራቸው ትምህርቶች ዙሪያ የተጻፉ ትልልቅ መጽሐፎችን ቀርቶ ትንንሾቹን እንኳን ለማንበብ የሚጓጓ ተማሪ ለማግኘት መሻት ጉም ለመዝገን እንደመጣር ያለ የዋህነት ነው፡፡ የከፍተኛ ተቋማት መምህራንም በሚያስተምሯቸው ትምህርቶች ዙሪያ በጥቂት ገጾች የተቀነበበች ማብራሪያ (hand out) በመስጠት ለተማሪዎቻቸው ያለማንበብ ፍላጎት የበኩላቸውን አስተዋጽዖ ያበረክታሉ፡፡ በዚህ መንገድ የሚመረቱ ምሁራን ያቺን የተመጠነች ማብራሪያ በመሸምደድ የሚያፈሩት ዕውቀት ፅንሰ ሐሳባዊ (conceptual) ሊሆን ቀርቶ (definition) ስለተማሩት ጉዳይ እንኳን ትክክለኛ ብያኔ መስጠት የማያስችላቸው በመሆኑ፣ ወደሥራ ዓለም ወይም ወደመምህርነት ሲሸጋገሩ በሁለቱም በኩል የማይሳካላቸው የመሆናቸው ነገር የቅርብ ጊዜ ምሩቃንን በመመልከት ከአንጀት መመሥከር ይቻላል፡፡

በመሠረቱና እንደእውነቱም ከሆነ አንባቢ ማኅበረሰብ ማፍራት ለአገር ዕድገት ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡ ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ በዚህ የታደለች አገር መሆንዋን መጠራጠር የሚቻል ይመስለኛል፡፡ ይህንን ለማለት የሚያበቁ በርካታ እውነታዎች አሉ፡፡ እስኪ ለምሳሌ የሀገራችንን የጋዜጦች ሥርጭት ብዛት አንስተን የንባብ ባህላችንን እንታዘበው፡፡ በኢትዮጵያ የመንግሥት ጋዜጦች የሆኑት እነ ‹አዲስ ዘመን› እና ‹Ethiopian Herald› የመሳሰሉት ጋዜጦች የሥርጭት ብዛታቸው እስከ 50,000 የሚደርስ ቢሆንም፣ በአብዛኛው በመንግሥት በጀት የሚሰራጩ እና በቀሪው ደግሞ የጨረታ ማስታወቂያ በሚፈልጉ አካላት የሚሸመቱ በመሆኑ፥ በእኔ በኩል የአንባቢዎችን ቁጥር ለመገመት እንደናሙና ልጠቀምባቸው ይከብደኛል፡፡

ነገር ግን በከፍተኛ ተነባቢነት ደረጃ ላይ ይገኛሉ የሚባሉትን የግል ጋዜጦች አንባቢ ብዛት በመመልከት የአንባቢነታችንን ደረጃ መገመት ይቻላል የሚል እምነት አለኝ፡፡ ‹አዲስ አድማስ› በኢትዮጵያ ከፍተኛ አንባቢ ያለው የግል ጋዜጣ እንደሆነ ይነገራል፡፡ የከፍተኛ ዕትሙ ብዛት በተለምዶ 20,000፣ አነጋጋሪ ዜና ሲኖር ደግሞ 40,000 በሳምንት ብቻ ይወሰናል፡፡ ከ80 ሚሊዮን የሚበልጥ ሕዝብ በሚኖርባት አገር ከፍተኛ የተባለው የጋዜጣ አንባቢዎች ቁጥር ይህን ያህል ብቻ ቢሆንም የኢትዮጵያን ግማሽ ያህል ሕዝብ ብቻ የሚኖርባት ጎረቤታችን ኬንያ ግን ‹Daily Nation› የተባለው ዕለታዊ ጋዜጣዋ ብቻ በየቀኑ ከ200,000 በላይ አንባቢዎች እንዳሉ ጥናቶች በድርሳናቸው ያወሳሉ፡፡

ምሁራን በአገራቸው ውስጥ የሚከወኑ ክስተቶችን ቀርቶ ዓለማቀፋዊ ጥቅል ጉዳዮችን በተመለከተ ወቅታዊ መረጃ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ የአንድን አገር ሕዝብ የሚመሩት ምሁራን እንደመሆናቸው እነሱ በንባብ ባሕልና በዕውቀት ልቀው ካልተገኙ የአገሪቱ ማኅበረሰባዊ ንቃትም ሆነ ብልፅግና ቀርፋፋ እንደሚሆን ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ ሆኖም በአገራችን እውነታው የተገላቢጦሽ መሆኑን ተመልካች ይፈርዳል፡፡

## ጸሐፊነት

ከምሁራን የሚጠበቀው አንባቢነት ብቻም አይደለም፡፡ ዕውቀታቸውን አፍነው የሚቀመጡ "የጋን መብራት" አለመሆናቸውን የምናረጋግጠው በሚጽፏቸው ጽሑፎች ነው፡፡ ምሁራን በተለይ በተማሩበትና በተመራመሩበት ዘርፍ ያሉ አዳዲስ ነገሮችን በጽሑፍ ለአደባባይ የማብቃት ኃላፊነት አለባቸው፡፡ አሁንም እንዳለመታደል ሁኖ፣ በአገራችን የምንመለከተው ይህንን አይደለም፡፡ በርካታ ምሁራን በራሳቸው ዓለም ተጠምደው ዕውቀታቸውን ከማጋራት የተቆጠቡ ይመስላሉ፡፡ የተለያዩ ጥናቶችን ከሚያካሂዱት ውስጥም ጥቂት የማይባሉቱ ጥናቱን የሚያዘጋጁት የምርምር ድጎማ (research grant) ለማግኘት ሲሉ ብቻ ሊሆን እንደሚችል አፍን

ሞልቶ መናገር ይቻላል፡፡

አንዳንድ ሀገራት የዩንቨርስቲ ፕሮፌሰሮቻቸው በዓመት ውስጥ የተወሰኑ ጆርናሎችን ካላሳተሙ፣ ጥናቶችን ካላካሄዱ ማዕረጋቸውን የሚቀሙበት መመሪያ አላቸው፡፡ ለእነሱ እንደመታደል ለአካዳሚያዊ ዕድገት ግን እንዳለመታደል ሆኖ የእኛ ሀገሮቹ ምሁራን እንዲህ ዓይነቱ ሥጋት የለባቸውም፡፡ በድሮ ዕውቀታቸው ዛሬም ድረስ ይሾማሉ፤ ይብዛም ይነስም መሃያም ያገኙበታል፡፡

ሌላውና በጣም አሳሳቢው ጉዳይ ደግሞ ተመራቂዎች በሰው ሥራ ለመመረቅ የሚያደርጉት ጥረት ነው፡፡ ጉዳዩ የሰው ሥራ የኔ ነው ብሎ ማቅረብ (plagiarism) ነው እንዳይባል በማይመች መልኩ የጥናቱ ውጤት ባለንብረት - ተማሪዎቹ ራሳቸው ናቸው፡፡ ነገር ግን እነርሱ አይሠሩትም፡፡ አንድ እኔ በቅርበት የማውቀው ሰው ብቻውን በጥቂት ዓመታት ውስጥ ከ25 ለሚበልጡ ተማሪዎች የመመረቂያ ጽሑፍ እንዳዘጋጀላቸውና እንዳስመረቃቸው ነግሮኛል፡፡

ነገሩ የሚያስደነግጣችሁ እንዳላችሁ ሁሉ፥ ‘ታዲያ ይሄ ምኑ ያስገርማል?’ ብለው በቀላሉ የሚያልፉትና ይህ ዓይነቱን ውስልትና እንደግሩም ባህል የሚቆጥሩ እጅግ ብዙ ሰዎች እንዳሉ መረዳት የገባንበትን አጣብቂኝ ይበልጥ ለመገንዘብ ይረዳናል፡፡ አሁን፣ አሁን ሥራ አጥ ምሩቃን ብቻ ሳይሆን ጥቂት መምህራንም ሳይቀሩ የተመራቂ ተማሪዎችን ጽሑፍ በማሰናዳት ሥራ ተጠምደዋል፡፡ ነገሩ በጣም አዋጭ ነው፡፡ የሚያዋጣው ግን ጊዜያዊ ጥቅምን ከማጋበስ አንፃር እንጂ ለተመራቂውም ሆነ ለአስመራቂው የኋልዮሽ መዘዝ አለው፡፡

በእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥሩ ዐረፍተ ነገር መሥራት የማይችል ተማሪ የሚያስገርም ጥናታዊ ጽሑፍ ይዞ ቢቀርብ መደነቅ ብቻ ሳይሆን መጠየቅም ተገቢ ነው፡፡ ምክንያቱም ከጀርባው ‹‹የኮንትሮባንድ ጥናት አዘጋጆች›› አሉና፡፡ ይህ ዓይነቱ ድርጊት በመመረቂያ ጽሑፎች ብቻ ሳይሆን ጥቂት ማርክ በሚያስገኙ የቤት ሥራዎችም ሳይቀር የተለመደ እየሆነ መምጣቱ የአደባባይ ምሥጢር ከሆነ ዋል አደር ብሏል፡፡

ተማሪዎችም ባልሠሩት ሥራ የመመዘናቸውና ብቁ ናቸው ተብለው የመመረቃቸው ነገር የተማሩ ማይማንን በመፍጠሩ ረገድ የበኩሉን ድርሻ እያበረከተና በውጤቱም ሀገርን እያጠፋ ነው፡፡ በመሠረቱ ጥናቱ የተሠራላቸው ብቻ ሳይሆኑ ጥናቱን ለገንዘብ ሲሉ የሚሠሩትም እንዲያው ናቸው፡፡ መማር ማለት ብቁ ዜጋን ለማፍራት የኃላፊነት ስሜት ማዳበር እንጂ “እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል” ማለት አይደለምና፡፡

## ምሁር /የተማረ/ ማነው?

‘የተማረ’ የሚለው ቃል የሚወክለው ‹የሰውዬውን የትምህርት ደረጃ ወይስ ዕውቀቱን እና ክህሎቱን?› ለሚለው ጥያቄ መልስ መስጠት ይቸግር ይሆናል፡፡ ነገር ግን በየትኛውም መለኪያ ሰዎች ትምህርት እንዲቀስሙ የሚደረገው በቁጥር የሚለካ፣ የሆነ ደረጃ ላይ የሚያደርስና መድረሳቸውንም ለማወጅ የሚያስችል ሳይሆን የትምህርት ደረጃቸው ባደገ ቁጥር በተማሩበት ዘርፍ ከሌላው የበለጠ ዕውቀትና ክህሎት በማፍራት ማኅበረሰባቸውን ማገልገል የሚያስችል፤ ብሎም በየዘርፉ የመሪነትን ሚና እንዲጨብጡ የሚያስችል ነው፡፡ ምሁራን በከፍተኛ ተቋማት ውስጥ ተማሪ በነበሩበት ወቅት ከሚኖራቸው ተወዳዳሪነት የበለጠ በሥራው ዓለምም ሊኖራቸው ይገባል፡፡የተማረ የሚያሰኛቸውም ይኸው ይመስለኛል፡፡

ስለዚህ ምሁራን የተማረ ለመሰኘት የመመረቂያ ‘ግሬድ’ ብቻ ሳይሆን በቂ የሥራ ብቃት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ሮናልድ ናሽ የተባሉ አሜሪካዊ ተመራማሪ የተማሩ ለመሰኘት ፊደል መቁጠር ብቻ አይበቃም ብለው ይከራከራሉ፡፡ ‹‹ትምህርት ቤት ከመሄድ ባሻገር የባሕል እና የሞራል ዕውቀትን ማፍራት ያስፈልጋል›› ብለዋል፡፡ የባሕልና የሞራል ዕውቀት ለማፍራት ቀጥተኛ የተምሮ ማስተማሩ ሂደት የሚያደርገው አስተዋፅዖ ግን ውሱን ነው፡፡ ዜጎች በጠንካራ ማኅበራዊ ተሳትፎ ባሕላዊና ሞራላዊ ዕሴቶችን ማዳበር ይገባቸዋል፡፡ ሞራላዊ ዕሴቶችን ማዳበር ይገባቸዋል፡፡ በዚህም ምሁርነታቸውን ከወረቀት በላይ ፋይዳ ያለው ነገር ማድረግ እንዲችሉ ይረዳቸዋል፡፡

## ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እውነተኛ ምሁራንን ለማፍራት ምን ያድርጉ?

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በትምህርት ሚኒስቴር የአዳዲስ ምሩቃን የብቃት ማረጋገጫ ፈተናዎች እየተበራከቱ መጥተዋል፡፡ እንዲህ ዓይነቶቹ ፈተናዎች ምክንያታቸውና ይዘታቸው ይለያይ እንጂ በተለያዩ ዓለማት የተለመዱ ናቸው፡፡ ለምሳሌ በምዕራብ አገሮች ዩንቨርስቲ የትምህርት ዕድል ለማግኘት የዲግሪ ማስረጃ ብቻ ይዞ መቅረብ አይበቃም፡፡ ተጨማሪ እንደ GMAT (Graduate Management Admission Test)፣ SAT (Scholastic Aptitude Test) እና ሌሎችም እንደ TOEFL የመሳሰሉትን የቋንቋ ፈተናዎችን

ማለፍ ግዴታ ነው፡፡ እነዚህ አገራት መመዘኛዎቹን የሚያስቀምጡት ለሦስተኛው ዓለም ሰዎች ብቻ አይደለም፡፡ ከቋንቋ ክህሎት ፈተናው ውጪ ያሉትን ለራሳቸው ዜጎችም ጭምር ነው፡፡ በርግጥ በእኛም ሀገር የመጀመሪያና የሁለተኛ ዲግሪ ለማጥናት የመግቢያ ፈተናዎች አሉ፡፡ የኛዎቹ የሚለዩት፣ በየተቋማቱ ያሉትን ውሱን ቦታዎች ለማከፋፈል እንጂ በርግጥም የተማሪውን ብቃት ለመመዘን አይመስልም፡፡

በትምህርት ሚኒስቴር ሥር ያሉት የሙያ ብቃት ምዘናና ማረጋገጫ ማዕከላት የTVET ተማሪዎች በመደበኛውም ይሁን በሌላ ፕሮግራም ከተመረቁ በኋላ CoC የሚባል የቃልና የተግባር ፈተና እና የዲግሪ ተማሪዎችም ከመመረቃቸው በፊት ሀገር አቀፍ ፈተናዎችን እንዲወስዱ የሚያደርጉበት አካሄድ እየተፈጠረ ነው፡፡ በርካታ ምሁራን ዕውቅና ያላቸው ተቋማት አምነውባቸው ያስመረቋቸውን ተማሪዎች የብቃት መመዘኛ ፈተና መስጠት በተቋማቱ ላይ ጥርጣሬ ማሳደር ነው በማለት ቢከራከሩም፥ በተለይም ቀደም ሲል ተግባር ላይ በዋለው የCoC ፈተና ላይ የመንግሥትና የግል ተቋም ሳይባል ከ20 በመቶ ያልበለጡት ተፈታኞች ብቻ የማለፋቸው ምሥጢር አጠያያቂ ሆኖ ሰንብቷል፡፡ አንድም የትምህርት አሰጣጡ ሥርዓት በሀገር አቀፍ ደረጃ ችግር አለበት፤ አሊያም ፈተናው ደረጃቸውን የሚመጥን አይደለም ማለት ነው፡፡ ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን ማለፍ ያልቻሉት ተፈታኞች በገበያው ውስጥ የሚፈለግባቸውን ብቃት አለመያዛቸው ሊሠመርበት የሚገባ መራራ እውነት ነው፡፡ (ፈተናው ገበያውን የሚመጥን ነው እስካልን ድረስ!)

በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ እየጻፍኩ እንደሆነ ሹክ ያልኩት አንድ የቅ/ማ/ዩ/ኮ መምህር ከአንድ የመንግሥት ከፍተኛ የትምህርት ተቋም (ዩንቨርስቲ) የተመረቀች ተማሪ በተመራቂዎች መጽሔት ላይ ከፎቶዋ ግርጌ ያሠፈረችውን ማስታወሻ (የመጨረሻ ቃል ይሉታል) ነገረኝ፡፡ *"ምሥጋና ሳይማሩ ላስተማሩኝ መምህሮቼ"* ይላል፡፡ ከዚህ አባባል በስተጀርባ ብዙ እውነቶች አሉ፡፡ ልብ ያለው ልብ ብሎ ‹ሳይቃጠል በቅጠል› እንዲሉ ነውና የማስተካከያ እርምጃ ባፋጣኝ ቢወሰድ ከተጨማሪ ጥፋት እንድናለን ብዬ አምናለሁ፡፡

ከትምህርት ሥርዓቱ እና ተጓዳኝ ጉዳዮች ባልተናነሰ የመምህራን ብቃት የአዳዲስ ምሩቃንን ብቃት የመወሰን ድርሻ አለው፡፡ ዛሬ ዛሬ በየከፍተኛ ተቋማቱ የምናገኛቸው በርካታ መምህራን በኃላፊነት ስሜት ማጣት፣ በዕውቀት ማነስ፣ በተነሳሽነት ማሽቆልቆል ወይም በሌላ ምክንያት የዕለት ግዴታቸውን ለመወጣት ከመፈለግ በበለጠ በተቆርቋሪነት ስሜት ኃላፊነት የሚሰማው የተማረና የተመራመረ ብቁ ዜጋ ለመፍጠር ሲጥሩ አይስተዋሉም፡፡ እንዲያውም አሁን አሁን በቀልድ እየተነገረ እንዳለው ተማሪዎች መምህሮቻቸውን አርአያ ማድረግ ሲገባቸው አንዳንድ መምህራን ተማሪዎቻቸውን አርአያ በማድረግ የሱስ ማዘውተሪያ ሥፍራዎች ላይ ሳይቀር ከገዛ ተማሪዎቻቸው ጋር የሚሰባሰቡበት አጋጣሚ የተለመደ ሆኗል፡፡ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የእነዚህን መምህራን ተነሳሽነት ለመጨመር፣ ዕውቀታቸውን ለማሳደግና የገቡበት የሞራል ውድቀትና የሥራ መንፈስ መቀዛቀዝ ተሰምቷቸው ኃላፊነት መሸከም የሚችሉ - የወረቀት ሳይሆን፣ እውነተኛ ምሁራንን መፍጠር የሚያስችላቸውን ስትራቴጂ መቅረፅ ለነገ ሊያሳድሩት የማይገባ የቤት ሥራቸው መሆኑን ሊረዱ ይገባል፡፡ ያኔ ታዲያ አሁን የምንተማማባቸው ለጆሮ ሳይቀር የሚዘገንኑ ምሁር ነክ ጥያቄዎችና አስተያየቶችና እንዲሁም ቅሬታዎች በአንዴም ባይሆን ቀስ በቀስ ይወገዳሉ፡፡ ለዚያ ጊዜ ያድርሰን፡፡

***A little knowledge is a dangerous thing.***
***Drink deep, or taste not the Pierian spring;***
***There shallow draughts intoxicate the brain;***
***And drinking largely sobers us again.***

***Alexander Pope*** **(1688-1744) English poet and satirist.**

He who dares to teach must never cease to learn.

***Unknown Source***